بسم الله الرحمن الرحيم

# አወዛጋቢዉ የመዉሊድ በዓል

## ዝግጅት

ዓብዱለጢፍ መሀመድ
ኢልያስ አህመድ
ሳላህ አህመድ

ምስጋናና ውዳሴ ለአላህ ነው። አላህ በታላቁ ነቢይ ላይ ሰላምና እዝነቱን እንዲያወርድባቸው እንጠይቃለን፡፡

ከመሀይምነት ጽልመት ወደ ኢማን ብርሃን ያወጡን ዘንድ ለተላኩት ታላቅ ነቢይ፤ ለእሳቸዉ ያለን ውዴታና አክብሮት እጅግ የላቀ ነዉ ፤ በእሳቸዉ ፈለግ ላይ እንዲያፀናን አላህን እንማፀነዋለን።

አዎን! የእኚህን ታላቅ መልዕክተኛ ቃል እንድናከብር፣ ፋናቸውን እንድንከተል፣ ስብናቸውን እንድንላበስለ፣ ከልጅ፣ ከእናት፣ ከአባት፣ ከሰዎች በሙሉ አስበልጠን! እንድንወዳቸው በሱረቱ ተውባ ምዕራፍ፣ ቁጥር 24 በአፅኖት ተመክረናል።«አባቶቻችሁና ወንዶች ልጆቻችሁ፣ ወንድሞቻችሁም፣ ሚስቶቻችሁም፣ ዘመዶቻችሁም፣ የሰበሰባችኋቸው ሀብቶችም፣ መክሰሩዋን የምትፈሩዋት ንግድም፣ የምትወዷቸው መኖሪያዎችም እ ናንተ ዘንድ ከአላህና ከመልክተኛው፣ በርሱ መንገድም ከመታገል ይበልጥ የተወደዱ እ ንደኾኑ አላህ ትዕ ዛዙን እ ስከሚያመጣ ድረስ ተጠባበቁ በላቸው፤አላህም አመፀኞች ሕዝቦችን አይመራም፡፡»

ይህ አንቀጽ ልጆቻችንን፣ ሚስቶቻችንንና፣አባቶቻችንን ከምንወደዉ የበለጠ ነቢዩን (ሠ.ዐ.ወ) መውደድ እንዳለብን ያስገነዝበናል፤ ይህ ም ብቻ አይደለም፤ ይህን ላላደረጉ ‹‹ተጠባበቁ!›› በማለት ዝቶባቸዋል፤ አመፀኞች መሆናቸውንም ገልጾልናል፡፡ ግን የነቢዩ እውነተኛ ወዳጆች እነማናቸው? በእሳቸው መመሪያ ላይ የፀኑት፣ ትዕዛዛቸውን የተገበሩት፣ ከፈለጋቸው ጭራሽ ያላፈነገጡት፤ ወይስ ‹‹ነቢዩን በመውደድ›› በሚል ሽፋን ዝንባሌያቸውን በመከተል ያማራቸውን የፈጠራ ተግባር የሚያራምዱት?! እስኪ የእውተኛ ውዴታን መመዘኛ አስመልክቶ የቁርዓንን መመዘኛ እናስተውል፡-

«አላህን የምትወዱ ከሆናችሁ ተከተሉኝ፤ አላህ ይወዳችኋልና፤ ኀጢአቶቻችሁንም ለናንተ ይምራልና፤አላህም መሓሪ አዛኝ ነው፡- በላቸው፡፡»[1]

ታዲያ ነቢዩን መከተል የዉዴታችን መለኪያ እንደሆነ ከተረዳን በዲን ጉዳይ ላይ እሳቸው የሰሩትን መስራትና የተዉትንም መተው ይጠበቅብናል።ወደ ጌታችን የሚያቃርቡንን መንገዶችና የእርሱን ውዴታ እነድንጎናፀፍ የሚያስችሉንን የአምልኮ ተግባራት ያለመለኮታዊ መመሪያ በዘፈቀደ ልናውቃቸውና ልንተገብራቸዉ አንችልም! ለህዝቦቻቸው አርዓያና ተምሳሌት የሆኑ ነቢያት የመላካቸው ዋነኛ ምክንያትም ይህ ነዉ።

[1] (አሊ-ዒምራን፡ 31)

የተከበሩት መልዕክተኛ እንዲህ ይላሉ:- **‹‹ለህዝቦቹ የሚያውቀውን መልካም ነገር መጠቆምና ከሚያውቅላቸው ክፉ ነገር ማስጠንቀቅ ግዴታ ቢሆንበት እንጂ ከእኔ በፊት (አንድም) ነቢይ አልነበረም››**[2] **ስለዚህም ተወዳጁ ነቢያችን በዲን ጉዳይ ላይ ጠቃሚ ሆኖ ሳያስተምሩት ያለፉት ርዕስ የለም !!**

ወደ አላህ ውዴታ የሚያቃርቡንን የአምልኮ ተግባራት በሙሉ በጌታቸው መመሪያ መሰረት ቅንጣት ያክል ሳያጓድሉ በአግባቡ አስተላልፈዋል።

ስለሆነም በዲን ጉዳይ አዲስ የፈጠራ ተግባራት በሙሉ[3] በተለያዩ ቁርአናዊና ሀዲሳዊ መረጃዎች መሰረት የተወገዙ ናቸው፤ አላህ በተከበረው ቁርአኑ ይህንን ጠቁሞነናል፤ የአማርኛው ትርጉሙ :- **‹‹አላህ ከሃይማኖት በርሱ ያልፈቀደውን ለእነርሱ የደነገጉ ተጋሪዎች አሏቸውን?!››**[4]

ከዚህ አንቀፅ አላህ ያልፈቀደውን ዲን መደንገግ እንደማይቻል እንረዳለን።

- ረሱል እንዲህ ብለዋል:- **‹‹በዚህ በጉዳያችን (በዲናችን) ከእርሱ ያልሆነን ነገር የፈጠረ (ስራው) ተመላሽ ነው።››**[5] በሌላም ዘገባ ላይ እንዲህ ይላሉ:- **‹‹ትዕዛዛችን የሌለበትን ስራ የሰራ (ስራው) ተመላሽ ነው።››**[6]

- እንደዚሁም በጁሙዓ ኹጥባቸው መግቢያ ላይ የሚከተለውን ይሉ እንደነበር ተዘግቧል:- **‹‹የንግግር ሁሉ የተሻለው የአላህ መፅሐፍ ነው፤ ከመመሪያ ሁሉ በላጩ የሙሀመድ (ሰ.ዐ.ወ) መመሪያ ነው፤ የነገሮች ሁሉ መጥፎ አዳዲስ ነገሮች ናቸው፤ ሁሉም የፈጠራ ተግባር ጥመት ነው…››**[7]

- ይህንንም ጉዳይ በአደራ አፅንተው ነበር ወደ አኺራ ያለፉት፤ እንዲህም አሉ :- **‹‹የእኔን እና ቅን፣ የተመሩ የሆኑ ምትኮቼን ፈለግ በመከተል ላይ አደራችሁን! (ይህችን ፈለጌን) አጥብቃችሁ ያዟት! አደራችሁን! አዳዲስ ነገሮችን ተጠንቀቁ! አዲስ ነገር ሁሉም ፈጠራ ነው፤ ሁሉም ፈጠራ ደግሞ ጥመት ነው››**[8]

- በሌላም ሃዲሳቸው እንዲህ ይላሉ:- **«የርሱን ፈለግ የሚይዙና ትእዛዙን የሚከተሉ ረዳቶችና ጓደኞች ከህዝቦቹ ቢኖሩት እንጂ አላህ ነቢይን አልላከም ፤ ከዚያም ከእነሱ በኋላ የማይሰሩትን የሚናገሩና ያልታዘዙትን የሚሠሩ ይተካሉ። (እነኚህን) በእጁ የታገላቸው ሙዕሚን ነው፤ በምላሱም የታገላቸው ሙዕሚን ነው፤ በልቡ የታገላቸውም ሙዕሚን ነው፤ ከዚህ በኋላ የሰናፍጭ ፍሬ ያክል እንኳ ኢማን የለም»**[9]

ያልታዘዙትን የሚሠሩትን አስመልክቶ **‹የታገላቸው ሙዕሚን ነው›** ማለታቸው ያልታዘዝነውን ነገር ጥሩ ቢመስልም ከዲናችን በመቁጠር ለመስራት መሞከራችን ተገቢ ያለመሆኑን ነው፤ በ‹ምናስበት› ፈሊጥ ራሳችንን ለአደጋ መዳረግ አይኖርብንም!

- **ይህ ዲን የሞላ ነው!!** አላህ መሙላቱን በቁርዓን አውስቷል። መልዕክቱ በአማርኛ ሲተረጎም እንደሚከተለው ይነበባል:-

---

[2] ሰሂሀ ሙስሊም ቁጥር 1844 ከዓብዱላህ ኢብን ዓምር የተዘገበ ሀዲስ
[3] የፈጠራ(የቢድዓ) ተግባር ሁለት ዐይነት ነው፤**አንደኛው** ከነአካቴው ከሸሪዓ ምንም መሠረት የሌለው ሲሆን **ሁለተኛው** ደግሞ ተግባሩ በጥቅሉ ሸሪዓዊ ድንጋጌ ቢኖረውም አተገባበሩ ላይ በጊዜ፣ ወይም በቦታ፣ ወይም በመጠን(በቁጥር)፣ ወይም በሰበብ፣ ወይም በሆነ የአፈጻጸም ስርዓት ያለመረጃ ሲገደብ ፤ አሊያም ሸሪዓዊ ገደቡ ሲነሳ ነው። **ሁለቱም ዓይነቶች የተወገዙ ናቸው!**
[4] አል-ሹራ ቁ. 21
[5] አልቡኻሪ በቁጥር(2550) እንዲሁም ሙስሊም በቁጥር(1718) ከዓኢሻ ዘግበውታል።
[6] ሙስሊም በቁጥር(1718) ከዓኢሻ ዘግበውታል።
[7] ሙስሊም በቁጥር( 867 )ከጃቢር ኢብን ዐብዲላህ ዘግበውታል።
[8] አህመድ (4/126-127) ፣በአቡዳዉድ(4607)፣አቲርሚዚይ(2676)፣ኢብኑማጃህ(44) ከዒርባድ ኢብን ሳሪያ የዘገቡት ሀዲስ
[9] ሙስሊም በቁጥር (50) ዘግበውታል።

« ዛሬ[10] ሀይማኖታችሁን ለናንተ ሞላሁላችሁ፤ ጸጋዬንም በናንተ ላይ ፈጸምኩ፤ ለናንተምኢስላምን ከሃይማኖት በኩል ወደድኩ፡፡»[11]

ይህንንአንቀጽ አስመልክተው አል-ኢማሙ ማሊክ እንዲህ ይላሉ፡- ‹‹በኢስላም ውስጥ አዲስ ነገርን ፈጥሮ ጥሩ መስላ ከታየችው ነቢዩን መልእክታቸውን አጓድለዋል ብሎ ጠርጥሯል፤ ያኔ ዲን ያልነበረ ዛሬ ዲን አይሆንም!››

ከዚህአንቀጽ በኋላ የቁርዓን አንቀጽ ቢወርድም ግን በጣም ውስን ነው፡፡አንዳንድ ሰሃባዎችም የመጨረሻ ነው ይላሉ።የረሱል ምርጥ ሰሀቦችና ተተኪዎቻቸው ከላይ የተጠቀሰውን ነቢያዊ ፈለግ በመከተላቸው ቢድዓን ነቅፈውና ተዋግተው ዲናቸውን ከአዳዲስ ልጣፊዎች ጠብቀው አደራቸውን በአግባቡ ተወጥተዋል፡፡

- ታላቁ ሰሀቢይ ሁዘይፋ አብኑል የማን እንዲህ ይላሉ፡- ‹‹ማንኛውም የመልዕክተኛው ሰሃቦች ባልሰሩት የዒባዳ ተግባር አምልኮን አትፈፅሙ! የመጀመሪያዎቹ ለመጨረሻዎቹ ምንም አልተዉም!››[12]

- ዓብዱላህ ኢብን ዑመር እንዲህ ይላሉ፡- ‹‹ሁሉም የቢድዓ ተግባር ጥመት ነው! ሰዎች መልካም አድርገው ቢያየዩት እንኳ!››[13]

- አንድ ቀን አቡ ሙሳ አል-አሽዓሪ ወደ ዓብዱላህ ኢብኑ መስኡድ ቤት ይመጡና እንዲህ ይለዋቸዋል፡- ‹አሁን መስጂድ ውስጥ የሚነቀፍ ነገር ተመለከትኩ፡፡› ‹ምንድነው›? አሉ ኢብኑ መስዑድ፡፡‹በሕይወት ካለህ ታየዋለህ! ሰዎች መስጊድ ውስጥ ሆነው ክብ ሰርተው ተቀምጠው ሶላትን ይጠባበቃሉ፤ ከተሰበሰቡት አንዱ በእጁ ጠጠር ይዞ፡- አንድ መቶ ጊዜ ተክቢራ አድርጉ፣ አንድ መቶ ተስቢህ፣ አንድ መቶ ታህሊል እያለ ያዝዛቸዋል፡፡እነሱም መቶ፣ መቶ ጊዜ ይላሉ፡፡› ኢብኑ መስዑድም ‹ምን አልካቸው ታዲያ?› ብለዉ ይጠይቋቸዋል፡፡‹ምንም አላልኩም፣ የአንተን አስተያየት በመጠበቅ!› ኢብኑ መስዑድም ‹ታዲያ ለምን ወንጀላቸውን እንዲቆጥሩ በመንገር፣ በጎ ተግባራቸውን ግን አላህ ዘንድ እንደማያጡት ዋስ አትሆናቸውም?› ከዚያም ወደ መስጊድ ገቡ፡፡ወደተሰበሰቡት ሰዎች በመምጣትም ‹ምንድነው መሥራት የያዛችሁት? ወንጀላችሁን ቁጠሩ፣ ጥሩ ሥራችሁን ግን አላህ ዘንድ እንደማታጡት ቃል እገባላችኋለሁ፡፡የሙሀመድ (ሠ.ዐ.ወ) ኡመቶች! ለመጥፋት ምን አስቸኮላችሁ፡፡የነቢዩ (ሠ.ዐ.ወ) ሰሀቦች ሞልተዋል፤ የነቢዩም (ሠ.ዐ.ወ) ልብስ (ገና) አላለቀም፤ ዕቃቸው እንኳ አልተሰበረም፡፡ነፍሴ በእጁ በሆነችው ጌታ እምላለሁ! እናንተ ከነቢዩ (ሠ.ዐ.ወ) መንገድ የበለጠ የተመራችሁ ናችሁ ወይም የጥመት በር ከፋች ናችሁ?!› አሏቸው፡፡ሰዎቹም ‹አቡ አብዱራህማን እኛ እኮ ጥሩ አስበን እንጂ ሌላ አይደለም› አሉ፡፡ ‹ጥሩ እያሰቡ ግብ የማይመቱ ስንቶች አሉ?! ነቢዩ (ሠ.ዐ.ወ) እንደነገሩን፡- (ሰዎች ይመጣሉ፣ ቁርዓን ይቀራሉ፤ ግን ከጉሮሯቸው አይወርድም!) ምናልባት ብዙዎቹ ከእናንተ ሳይሆኑ አይቀሩም፡፡...› ከዚያ ጥለዋቸው ሄዱ፡፡[14]

## እነዚህ ጥቅሶችና መረጃዎች ከብዙ በጥቂቱ ናቸው፡፡

☞ አንዳንድ ሰዎች የቢድዓ መጥፎነት የሚያሳዩ ምረጃዎች ሲቀርቡላቸዉ ‹ቢድዓ ጥሩ ነዉ!› አይሉም፡፡ግን ከነዚህ ነብያዊ ዛቻዎች ለመዉጣት ሲፍጨረጨሩ ‹‹ሁሉም ቢድዓ ጥመት ነው!!›› የሚለውን ጥቅል ነቢያዊ መርሆ የሚፃረር ግንዛቤ ያንፀባርቃሉ፤ ‹‹ቢድዓ ሁለት ዓይነት ነው፡- ጥሩና መጠፎ›› ይላሉ!! ለዚህም አባባላቸው ድጋፍ ይሆናቸው ዘንድ ሁለት ‹‹መረጃዎችን!?›› ይጠቅሳሉ፡፡

---

[10] ይህ አንቀጽ የወረደው በ10ኛው አመተ-ሒጅራ በዙልሂጃ ወር በጁሙዓ እለት ነቢዩ ዓረፋ በቆሙበት ነው፤ ለዚህም አል-ቡኻሪ ቁጥር 45 እንዲሁም ሙስሊም ቁጥር 3017 ይመልከቱ፡፡
[11] ሱረቱል ማኢዳ ቁጥር 5
[12] አቡ ዳዉድና ሌሎች ዘግበውታል፡፡
[13] ኢብኑበጣህ፣አልላለካኢይና ሌሎችም በትክክለኛ ሰነድ ዘግበውታል፡፡
[14] አድዳሪሚይና ሌሎች ዘግበውታል፡፡

**የመጀመሪያዉ ማደናገሪያ (ሹብሀ)** - መልዕክተኛው ‹በኢስላም ውስጥ የጥሩ ፈለግ ፈር የቀደደ ለርሱ የዚህ(ስራ) እና በዚህ (እርሱ በቀደደዉ ፈር) የሚሰራ ሰው ሁሉ ምንዳ አለው።ይህም ከእነሱ ምንዳ ምንም ሳይቀነስ ነዉ፤ በኢስላም ውስጥም የመጥፎ ፈለግ ፈር የቀደደ ለርሱ የዚህ(ስራ) እና በዚህ (እርሱ በቀደደዉ ፈር) የሚሰራ ሰው ሁሉ ወንጀል አለበት- ከእነሱ ወንጀል ምንም ሳይቀነስ።›[15] ብለዋል፤ ይህ ደግሞ ቢድዓ ሁለት ዓይነት እንደሆነ ይጠቁማል›› ይላሉ!

## የዚህ ምላሽ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

1ኛ፡- ነቢዩ (ሠ.ዐ.ወ) ሲናገሩ ‹‹በኢስላም ውስጥ›› ማለታቸው እንደሚጠቁመው በንግግራቸዉ የፈለጉት በዲኑ ውስጥ ተደንግገው ያሉ መልካም ተግባራትን እንጂ እያንዳንዱ ሰው ጥሩ የመሰለውን ተግባር ይስራ ለማለት አይደለም።[16] ይህንን የሚያጎላው ደግሞ የሚቀጥለው ነጥብ ነው፡-

2ኛ፡- ነቢዩ (ሠ.ዐ.ወ) ይህንን ሀዲስ የተናገሩበት ምክኒያት ሰሃቦችን ሰደቃ እንዲሰጡ ሲያነሳሷቸው አንድ ሰሃብይ ቀድሞ በመስጠት ለሌሎቹ አርዓያ በመሆኑ ነው፤ ሰደቃ ደግሞ በሸሪዓ አስቀድሞ የተደነገገ ተግባር ነው።ስለሆነም አዲስ ፈጠራ ዲኑ ውስጥ ለሚጨምሩ ሰዎች በፍፁም ማበረታቻ ሊሆን አይችልም።

**የመጀመሪያዉ ማደናገሪያ (ሹብሀ)** - ‹‹ሰዎች የተራዊህን ሰላት ተለያይተው በሚሰግዱ ጊዜ ኸሊፋው ዑመር(ረ.ዐ) ተሰባስበው እንዲሰግዱ ካደረጓቸው በኋላ "ምነኛ ያማረች ፈጠራ ናት!"[17] ብለዋል።ስለዚህ ከቢድዓም ያማረ ቢድዓ አለ ማለት ነው! ይላሉ።

## የዚህም ምላሽ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

1ኛ፡- የተራዊህ ሰላት ሱና እንጂ ቢድዓ አይደለም! ነቢዩ (ሠ.ዐ.ወ) የተወሰኑ ቀናት ሰርተው አቁመውታል፤ ምክንያታቸውንም ተናግረዋል፡- ዋጂብ (ግዴታ) እንዳይሆንብን ፈርተው ነው[18]፣ ግን ከአላህ የሚተላለፈዉ ወህይ ከነቢዩ (ሠ.ዐ.ወ) በኋላ ስለማይመጣ በዑመር ጊዜ ዋጂብ እንዳይሆንብን የሚፈራበት ምክንያት አልነበረም፤ ስለሆነም ነቢዩ (ሠ.ዐ.ወ) የጀመሩትን ሥራ ዑመር ቀጠሉት፣ ይህን ይበልጥ የሚያብራራው የሚቀጥለው ነጥብ ይሆናል፡-

2ኛ፡- በዲናችን የተከለከለዉ ቢድዓን መስራት ነዉ እንጂ ቢድዓ የሚለውን ቃል መጠቀም አይደለም።ቢድዓ እንደሌሎች ብዙ ቃላት ሸሪአዊና የቋንቋ ትርጉም አለው።ተቋርጦ እንደ አዲስ በመጀመሩ፤ ዑመር የፈለጉት ቋንቋዊ ትርጉሙን ነው።የሰሩትም ሥራ ሱናና መሰረት ያለው እንጂ አዲስ ፈጠራ አልነበረም።

3ኛ፡- ዑመር የሠሩት ሥራ በሰሀቦች ሁሉ ስምምነት የፀደቀ የኹለፋዎች ፈለግ በመሆኑ በሸሪዓ ቢድዓ አይባልም!

ታዲያ ከላይ በተጠቀሱት አስረጂዎች የተኮነነው **በዲን ስም የሚተገበረው የቢድዓ ዓይነት** ነው እንጂ አንዳንድ ሰዎች ‹አዲስ ፈጠራ ማምጣት ይቻላል!› ብለዉ ለመሞገት ሲፈልጉ የሚጠቅሷቸዉ የቴክኖሎጂ የፈጠራ ውጤቶች አይደሉም።ነቢዩ (ሠ.ዐ.ወ) በዋነኝነት ለማስተማር የተላኩት እነዚህን ዝርዝር የዱንያ ጉዳዮች አይደለም፤ ለመዲና ገበሬዎችም ይህንን ምላሽ ሰጥተዋል፡- **"ስለ ዱንያ ጉዳያችሁ እናንተ ይበልጥ ታውቃላችሁ!"** [19]።ስለዚህ ቁርዓንን በአንድ ጥራዝ ማስቀመጥ፣

[15] ሙስሊም ቁጥር (1017)
[16] የሀዲሱን ማብራሪያ በ(ቱህፈቱልአህወዚ)ይመልከቱ።
[17] አልቡኻሪ ቁጠር 2010
[18] አልቡኻሪ ቁጥር 2012 ይመልከቱ
[19] ሙስሊም ቁጥር (2363)

የእስር ቤቶችን ማዘጋጀት፣ ስፒከርን መጠቀም የመሳሰሉት በመልእክተኛው ዘመን ባይከሰቱም ወጥ የዒባዳ ተግባራት ሳይሆኑ ወደ ኢባዳ የሚያደርሱ አጋዥ መዳረሻዎች ስለሆኑ ነው።እነዚህ ደግሞ (መሳሊህ ሙርሰላ) ይባላሉ፣ ከቢድዓ ጋር በፍፁም አይገናኙም[20]

# መዉሊድን ማክበር በቁርአንና በሀዲስ ሚዛን ሲለካ

ዉድ አንባቢ! የመዉሊድ በአል በቁርአንና በሀዲስ መሰረት አለዉ ብሎ መድከም በከንቱ መኳተን እንደሆነ ልታዉቅ ይገባል፡፡ መውሊድ በነቢዩ (ሠ.ዐ.ወ) ጊዜ እንዳልነበረ ሁሉም ዑለማዎች ይስማማሉ፤ እንደዉም መውሊድ የሚያከብሩት ሳይቀሩ ይህንን እዉነታ አያስተባብሉም! በዓሉና ማክበር የተጀመረው ከአራተኛው ክ/ዘመን በኋላ እራሳችዉን **ፋጢሚዮች** ብለዉ ይጠሩ በነበሩት **የኡበየድ አልቀዳህ** ዘሮች ነበሩ።[21] እነዚህ ዑበይዲዮች ምንም እንኳ እራሳቸዉን ወደ ፋጢማ ቢያስጠጉም፤ ሰንካላ የሆነዉን የባጢኒያ አመለካከት በማስፋፋት፣የአላህን ትእዛዛት በመጣስ፣ በአመፀኝነት፣ድንበር በማለፍ፣ ዲንን በማዋረድ፣ የዲነልኢስላም ፋና እንዲጠፋ የቻሉትን ሁሉ በማድረግ፣ዑለማዎችን በመጨፍጨፍ የታወቁ ነበሩ።የኩፍር ንግግሮችን በመናገራቸዉ፣ አላህንና ነብያቶችን በግልፅ በመሳደባቸዉ፣ክልክሎችን ሀላል በማድረጋቸዉ ወዘተ .. ታላላቅ የኢስላም ሊቃዉንት ከኢስላም ምንም ድርሻ እንደሌላቸዉ ተናግረዋል።**ሰላሁዲን አል-አዩቢይ** (አላህ ይዘንለትና) ቁድስን ካስለቀቀ በኋላ እነሱንም አሸንፎ ሙስሊሙን ህብረተሰብ እፎይ አሰኝቷል።[22] ሆኖም ግን መውሊድን የጀመረው ሙዞፈር የተባለው ፍትሃዊ ንጉስ ነው።መውሊድ መጥፎ ቢሆን ኖሮ አይጀምረውም ነበር ይላሉ።መሊክ ሙዞፈርን (አቡ ሰዒድ ኮክበሪ) በዘመኑ የነበረው የታሪክ እና የጂዖግራፊ ሊቅ ያቁተል ሀመዊ ሲገልፀው “የሰው ንብረት ይዘርፋል፤ ግን ለድሃዎች ያበላል፣ ስራዎቹ ሁሉ ግራ የሚያጋቡ ናቸው” ይላል።መውሊድ የተጀመረው በፋጢሚዮች መሆኑ በግልፅ የታወቀ ቢሆንም አንቀበልም ካሉ የሚያመጣዉ ለውጥ የለም።ማንም ይጀምረው ነቢዩ (ሠ.ዐ.ወ) እና ኹለፋዎቻቸው ካልሰሩት ሌላ ሰዉ ቢሰራዉ ትርጉም አይኖረዉም። **ሰዎች በሀቅ ይመዘናሉ፤ ሀቅ ግን በሰዎች አይመዘንም!!**

→ የነቢዩ (ሠ.ዐ.ወ) ትክክለኛ የልደት ቀን በውልአይታወቅም። በሃዲስ የተገለጸው ሰኞ መወለዳቸው ብቻ ነው።በዝሆኑ ዓመት መወለዳቸውን የሚገልጽ የኢብኑ ዓባስ ሃዲስምአለ።ሆኖም የታሪክ ምሁራን በረቢዓልአወል እንደሆነ ይናገራሉ።በመካከላቸው ግን ከባድ ውዝግብ አለ፤ ለምሳሌ፡-አቡ ማዕሸረ ሲንዲ በረቢዕ 2 እንደተወለዱ ይናገራሉ፤ኢብኑኢስሃቅ በረቢዕ 12፣ ዋቂዲ በረቢዕ 10፣ ሱለይማን አል-መነሱርፉሪ በረቢዕ 9 እንደሆነ ይናገራሉ።ይህ ይመጨረሻዉ ጠንከር ያለ ዘገባ ነው።የሞቱበት ግን በረቢዕ 12 እንደሆነ ብዙሀኑ የታሪክ ዘጋቢዎች ጠቅሰዋል።ስለዚህ ሰዎች እያከበሩ ያለው የተወለዱበትን ቀን ላይሆን ይችላል የሞቱበትን ቀን ግን ነው!!

[20] የሁለቱን ልዩነት በተመለከተ ‹አልኢዕተሷም› የተባለውን የአል-ኢማሙ አሸሻጢቢይ መፅሀፍ ይመልከቱ።

[21] አልሚቅሪዚይ - አልመዋኢዝ ወል-ኢዕቲባር ቢዚክሪል ኺጠጢ ወልአሳር ቀፅ 1 ገፅ 490

[22] አልፈርቅ በየነል ፊረቅ ገፅ 266 የኡበይዲዮችን ታሪክ በተመለከተ አብዛኞቹ ታላላቅ የታሪክ ዘጋቢዎች በስፋት አስፍረዉታል ።

→ መውሊድን ማክበር ከላይ በተገለፀው መረጃዎች መሰረት የተወገዘ ነው፤ በመልዕክተኛው ዘመን ያልነበረ ነቢዩና (ሠ.ዐ.ወ) ከሊፋዎች ያልሠሩት የፈጠራ ተግባር ነውና!

→ አላህ በቁርዓኑ ውስጥ በነቢዩ ላይ የዋላቸውን የተለያዩ ፀጋዎች አውስቷል፤ ኢስራዕ እንዳስደረጋቸው፣ የቲም ሆነው እንዳስጠጋቸው፣ በሙእሚኖቹ ላይ ነቢይ አድርጎ እንደላካቸው . . . ሌሎችንም ውለታዎችን ያወሳል።እነዚህ ፀጋዎች በሳቸው ላይ ብቻ የተገደቡ ሳይሆኑ ለኡመታቸው ባጠቃላይ የተረፉ ታላላቅ ውለታዎች ናቸው። አንድም ጊዜ ግን ውልደታቸውን በዚህ መልኩ አልጠቀሰውም፣ አልተመፃደቀበትምም! እነዚህን አላህ የተመፃደቀባቸውን ታላላቅ ክስተቶች በየአመቱ ማክበር ያልተደነገገ ሆኖ ሳለ በቁርዐን ወይም በሀዲስ አንዴም ያልተወሳውን መውሊድን ማክበር እንዴት የተደነገገ ይሆናል?!

→ የክርስቲያኖች የቀን አቆጣጠር በዒሳ (ዐ.ሰ) ልደት ይጀምራል፤ ልደቱንም ያከብራሉ፡ የረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ዕውነተኛ ወዳጅ የሆኑት ቅን ሰሃቦች ግን በዑመር መሪነት የቀን አቆጣጠራቸውን የመሠረቱት በሂጅራ ክስተት ላይ እንጂ በመውሊድ አልነበረም።የአላህ መልዕክተኛ ከሺህ አራት መቶ ዓመታት በፊት እንዲህ ብለው ነበር፡- ‹‹ከእናንተ በፊት የነበሩትን (ሕዝቦች) ፈለግ ስንዝር በስንዝር፣ ክንድ በክንድ ትከተላላችሁ። የፍልፈል (ወከሎ) ጉድጓድ ቢገቡ እንኳ (ተከትላችሁ) ትገባላችሁ!›› ሰሃቦችም እንዲህ አሉ፡- ‹የሁዶችንና ክርስቲያኖችን?› ረሱልም፡- ‹(ታዲያ) ማንን?› አሉ።[23]

ከካፊሮች ጋር መመሳሰል ደግሞ ትልቅ ወንጀል ነው።‹‹ከሕዝቦች ጋር የተመሳሰለ ከእነሱ ነው›› ብለዋል መልዕክተኛው።[24] ስለዚህ ከዲን መሰረት በሌለው ነገር ካፊሮችን መፎካከር አይኖርብንም።

→ ከዑለማዎች እንደተገለፀልን ብዙ ሀዲሶችም እንደሚጠቁሙት እኛ ያሉን ኢዶች 7 ቀናት ናቸው፡ከነዚህ ውጭ ሌላ ዒዶች የሉንም። እነሱም ሳምንታዊ ዒድ ጁምዓ፣ ዓመታዊ ዒዶች ዒድ አልፊጥር፣ አድሃ፣ አያመተሽሪቅ፣ አረፋ (ለሁጃጆች) ናቸው።መግለፅ የፈለግነው ዲናዊ በዓሎችን ነው።ከነዚህ ሌላ ዲናዊ ዒዶች የሉንም።ሌላ የምንደሰትባቸው ቀናቶች ቢኖሩም የግላዊ ደስታ ቀናት ናቸው፡- እንደ ሰርግ፣ ልጅ ሲወለድ፣ የመሳሰሉት።መውሊድ በሙሉ ስምምነት ከነዚህ ውስጥ አይደለም።አነስ ኢበኑ ማሊክ ባወሩት ሀዲስ ነብዩ (ሰ.ዓ.ወ) እንዲህ ብለዋል ‹‹ወደ መዲና በመጣሁ ጊዜ የመዲና ሰዎች በጃሂሊያ ዘመን የሚዝናኑባቸዉ ሁለት በአላት ነበሩዋቸዉ።አላህም እነርሱን በተሻሉ ሁለት ዒዶች ቀየረላችሁ።የፊጥር ዕለት(ኢደልፊጥር) እንዲሁም የዕርድ ዕለት(ኢደልአድሀ)››[25]

→ * የመውሊድ አከባበር ስርዓትን በተመለከተ በድቤ፣ በጭብጨባና ጭፈራ የሚፈጸም አምልኮ በኢስላም አይታወቅም! እነዲያውም ከቀድሞ የመካ ሙሽሪኮች አምለኮ ጋር የሚያመሳስል ውግዝ ተግባር ነው።ይህ በቁረአን ተወስቷል፡-

“በቤቱ ዘንድም (በካዕባ) ስግደታቸው ማፏጨትና ማጨብጨብ እንጂ ሌላአልነበረም!”[26]

→ በዚህ በመውሊድ በዓል በአብዛኛው የተለያዩ የሽርክ ተግባራት፣ ወንድና ሴት መቀላቀልና የመሳሰሉት ጥፋቶች ሲተገበሩ ይታያሉ፤

---

[23] አል-ቡኻሪ (3269) ሙስሊም (6952) ከአቡሰዒድ አልኹድሪይ ዘግበውታል።
[24] አህመድ (5114) አቡዳዉድ (4033) ከኢብኑ ዑመር ዘግበውታል።
[25] አቡዳዉድ ዘግበዉታል አልባኒም ሰሂህ ብለዉታል
[26] ቀዱስ ቁርአን 08፡-35

ለእንዲህ ያሉ መዐቶች መድረክ የሆነው ይህ በአል በየትኛው ሚዛን ሲለካ ነው ‹‹ጥሩ ፈጠራ›› የሚባለው?ብዙዉን ጊዜ መዉሊድ ላይ የሚነገሩት በሀሰት የተሞሉ ትምህርቶች፣ መውዱዕ ሃዲሶች፣ድንበር ማለፍ (ጉሉዉ) ያለባቸዉ ዉዳሴዎች የነበባሉ።«በችግራችን ጊዜ ካንተ ሌላ ወደ ማን እንዞራለን?» የሚለዉን የቡሰይሪ ግጥም አይነት ጉሉዉን በመንዙማቸው ውስጥ ያካትታሉ።ነቢዩ (ሠ.ዐ.ወ) ከተናገሩት ጋር አስተያዩት፡-

‹‹ነሳራዎች የመርየምን ልጅ ኢሳን ከልክ በይ ከፍ እንዳደረጉት እኔንም ከፍ እንዳታደርጉኝ።እኔ (የአላህ) ባሪያው ነኝ ‹ባሪያውና መልእክተኛው› በሉ››[27]

# መውሊድን ማክበር ይፈቀዳል የሚሉ ሰዎች የሚያቀረቧቸው ማደናገሪያዎችና የተሰጧቸው ምላሾች

መውሊድን ማክበር ስለመፈቀዱ እንደ ‹‹መረጃ›› የሚጠቀሱት ነገሮች ላይ ያላቸው ግንዛቤ ከላይ ከተጠቀሱት ግልጽ መረጃዎች ጋራ የሚጋጩ መሆናቸው ግልጽ ነው፡፡

አብዛኛዎቹ ተራ ውዥምብሮች ናቸው! ዋና ዋናዎቹን እነሆ፡-

1ኛ፡- (ሙስሊሞች ከጫፍ እስከ ጫፍ የሚሰሩት ተግባር ነው።ኢብኑ መስዑድ በተናገሩት መውቁፍ በሆነ ሃዲስ መሰረት፡- “ሙስሊሞች ጥሩ አድርገው የተመለከቱት ነገር አላህ ዘንድ ጥሩ ነው።” ስለዚህ መውሊድ የብዙኃኑ ሥራ ነው፣ ልንቀበለው ይገባል) ይላሉ፡፡

## የዚህ ምላሽ እነደሚከተለው ይሆናል፡-

ይህ የኢብኑ መስዑድ ንግግር ትክክለኛ ቢሆንም ራሱ ተናጋሪው ኢብኑ መስዑድ በዚሁ ንግግሩ ላይ ‹‹በአቡበከር ኸሊፋነት ሶሃባዎች ተስማምተዋል›› ይላል።በዚህ መሰረት ብዙ ዑለማዎች ይህ ንግግር የሙስሊሞች ሙሉ ስምምነትን (ኢጅማዕን) የተመለከተ እንጂ ብዙኃኑን (ተራውን) ሕዝብ የተመለከተ እንዳልሆነ ይናገራሉ።መውሊድን ማክበር በሁሉም ስምምነት(ኢጅማዕ) የፀደቀ እንዳልሆነ ግልፅ ነው። እንዲያውም በተቃራኒው ቢድዓ ለመሆኑ የሁሉም ስምምነት ነው። ውዝግቡ ጥሩ ቢድዓ ነው ወይስ አይደለም በሚለው ነው።የቢድዓ ጥሩ እንደሌለ ደግሞ በብዙ መረጃዎች ተረጋግጧል።[28]

2ኛ፡- (አላህ በቁርዓኑ ላይ ነቢዩን እንድናከብርና እንድናልቅ ያዘናል። ስለዚህ እኛ ለእሳቸዉ ያለንን ክብር ልደታቸውን በማክበር እንገልፃለን!!) ይላሉ፡፡

## የዚህ ምላሽ እነደሚከተለው ይሆናል፡-

2.1፡- አላህ ነቢዩን (ሠ.ዐ.ወ) ያከበሩትን እና ከጎኑ የቆሙትን ሲያወድስ አያይዞ ከእሳቸዉ ጋር የተወረደውን ኑር(ብርሀን) የተከተሉትን ያወድሳል።[29]‹‹የተከተሉ›› የሚለው በራሳቸው ፈጠራ ውዴታን የገለፁ ማለት እንዳልሆነ ግልፅ ነው።እውነተኛ ተከታይ የሆነ ሰው አዛዡ ካለው ውጭ አይሰራም።

2.2፡- ሶሃባዎች በዚህ አንቀፅ የተወደሱት አምነው በመከተላቸው እንጂ መውሊድን በማድረጋቸው አይደለም።አስበውትም አያውቁም። ለነቢዩም (ሠ.ዐ.ወ) ይህንን ጥያቄ አላነሱም።‹ይህ የቁርዓን አንቀፅ

---

[27] አልቡኻሪይ (3445)
[28] ‹‹አል-ኢዕቲሷም››ን ይመልከቱ።
[29] (አል-አዕራፍ157)

እነሱን ሳይሆን እኛን መውሊድ የምናከብረውን ነው የሚመለከተው› ካላችሁ ግልፅ ጥመት ነው።ለዚህ ምንም ማስረጃ አያስፈልገውም።

2.3፡- ነቢዩን ማክበርና ማላቅ የሚረጋገጠው ትዕዛዛቸውን በማክበር፣ ፈለጋቸውን በመከተልና በመሳሰሉት እንጂ በአመት አንዴ እየተሰባሰቡ መውሊድን በማክበር አይደለም፤ በጥቅሉ እንደመረጃ የሚጠቀሱት አንቀጾች በተዘዋዋሪ የሚጠቁሙት ተቃራኒውን ነው!

3ኛ- (ነቢዩ (ሠ.ዐ.ወ) ሰኞን ይፆሙ ነበር።ስለዚህም ሲጠየቁ **‹‹ይህ የተወለድኩበት ቁርዐንም በኔ ላይ የተወረደበት ቀን ነው››** ብለዋል።በሰሂህ ሙስሊም ተዘግቧል።የነቢዩ (ሠ.ዐ.ወ) ልደት የተከበረ ባይሆን ባላከበሩት ነበር) ይላሉ።

## የዚህ ምላሽ እነደሚከተለው ይሆናል፡-

3.1፡- ነቢዩ የተወለዱበት ቀን ሰኞ መሆኑ የታወቀ ነው።ነገር ግን ሰኞን የፆሙት ቀኑን ለማክበር ነው የሚለው እሳቸዉ ያሉት አይደለም።እንዲያውም ነቢዩ (ሠ.ዐ.ወ) (በብዙ ሃዲሶች ላይ) ሰኞና ሐሙስን ለምን ይፆማሉ ተብለው ሲጠየቁ፡- **«እነዚያ ሁለት ቀናት ናቸው፤ ሥራዎች አላህ ፊት ለእይታ የሚቀርቡበት፤ ሥራዬ ፆመኛ ሆኜ (አላህ ዘንድ) እንዲቀርብልኝ እወድዳለሁ።»** ስለዚህ ትልቁ ዓላማቸው ሥራቸው አላህ ዘንድ ፆመኛ ሆነው እንዲነሳላቸው ነው።

ሰኞና ሐሙስ የተያያዙና ዓላማቸው አንድ የሆነ ፆሞች ናቸው።ነቢዩ (ሠ.ዐ.ወ) የአኺራ ጥቅምና ደረጃቸው ከፍ እንዲል የፆሙት እንጂ ወደ ዱንያ የመጡባትን ቀን ለማክበር ወይም ለማተለቅ ፈልገው እንዳልሆነ ራሳቸው ገልፀውታል።ነቢዩ (ሠ.ዐ.ወ) የተወለዱት፣ የተላኩበትና ያረፉበት ቀን ሰኞ መሆኑን ልብ እንበል።

3.2፡- ነቢዩ (ሠ.ዐ.ወ) የፆሙት ሰኞን እንጂ ረቢዕ 12ኛን ቀን አይደለም።ስለዚህ ረቢዕን ለመፆምም ሆነ ለማክበር ማስረጃ ሊሆን አይችልም።ሰኞን መፆም ማንም አይከለክለንም፣ ቢድዓ ነው ያለም የለም፣ በሃዲስ የተገኘ ነው።

3.3፡- ይህ መውሊድ ዒድ ተደርጎ ነው የተያዘው።ነቢዩ (ሠ.ዐ.ወ) ግን ሰኞን ፆም አድርገው ነው የያዙት።ፆምና ዒድ ደግሞ ተቃራኒ የሆኑ ተግባሮች ናቸው።ነቢዩ (ሠ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡-

**"የኢዳችሁን ቀን ፆም አድርጋችሁ አትያዙ"**[30] ለነቢዩ (ሠ.ዐ.ወ) ሱና እጅ ስጥ።ሰኞና ሐሙስን እንፁም፣ በአመት አንዴ ተሰብስበ በመብላትና በመጨፈር ግን መውሊድን አናክብር።

4ኛ፡- (ነቢዩ (ሠ.ዐ.ወ) የተለያዩ ክስተቶችን በማስታወስ ድሆችን ያበላሉ፣ ይፆማሉ፣ ያርዳሉ።ለዚህም የጁሙዐ የሀጅንና የአሹራን ተግባሮች መመልከቱ በቂ ነው።እንዲሁም አደም የተፈጠሩበት ቀን ስለሆነ ጁምዓን እንደምናከብር ሁሉ ነቢዩን (ሠ.ዐ.ወ) እያስታወስን የልደታቸውን ቀን ብናከብር ምንም ችግር የለበትም) ይላሉ።

## የዚህ ምላሽ እነደሚከተለው ይሆናል፡-

4.1፡- ነቢዩ (ሠ.ዐ.ወ) ክስተቶችን በማስታወስ ያረፉበትና ያበሉበት አንዳችም ክስተት የለም።በነቢዩ (ሠ.ዐ.ወ) ላይ ብዙ ጥሩ ክስተቶችን አልፈዋል።ለምሳሌ ኢስራእ፣ ሚዕራጅ፣ የበድር ዘመቻ፣ የመካ መከፈት፣ የቁርዓን መውረድ እና የመሳሰሉት ታላላቅ ክስተቶች

[30] ሃኪምና አሕመድ በዘገቡት ሰሂህ ሃዲስ

በነቢዩ (ሠ.ዐ.ወ) ዘመን ተከናውነው አልፈዋል።እነዚያን በማስታወስ ዓመታዊ የሆነ ዝግጅት አድርገው አያዉቁም! ለዚህም መረጃ ለማምጣት እንሞክራለን ካሉ ይሞክሩት፤ የኑህ እድሜ ቢሰጣቸውም መረጃ አያገኙለትም።

4.2፡- ሃጅ የተደረገው የሀጃርን፣ የኢብራሂምንና የኢስማኤልን ታሪክ ለማውሳትና ለማስታወስ ነው ብለው ካሰቡ ይህ ትልቅ ስህተት ነው። ነቢዩ (ሠ.ዐ.ወ) ያስተማሩን ሃጅ የተደነገገው የአላህን ውዳሴ ከፍ ለማድረግ ነው።ነቢዩ (ሠ.ዐ.ወ) እንዲህ ይሉናል **«ካዕባን መዞር፣ በሰፋንና በመርዋ መሀል መሮጥ፣ ጠጠርንም መወርወር፣ የተደነገጉት የአላህን ውዳሴ ከፍ ለማድረግ ነው»**[31]

የህንን አላህን ለማስታወስ የተደነገገ ዒባዳ ‹ታሪኮችን ለማስታወስ የተደነገገ ነው› ይላሉ።አላህ ትክክለኛውን መንገድ ይምራቸው። ደግሞም ዒባዳን ለማጽደቅ በቂያስ ላይ መመርዝ እንደማይቻል የታወቀ ነው።

4.3፡- ዓሹራንም በተመለከተ አሹራ መቼ እንደሆነ ይታወቃል፣ መውሊድ ግን ቀኑ እንኳ በትክክል አይታወቅም።እኛም አሹራን አትፁሙ አላልንም፣ መፆምና ማክበር የተለያዩ ነገሮች ናቸው።ነቢዩ (ሠ.ዐ.ወ) ሳዘዙን ተግባሮች ለሰለዋትና ለዚክር ራሳችንን እናዘጋጅ።

4.4፡- ጁምዓን የምናከብረው አደም የተፈጠረበት ቀን ስለሆነ እንደሆነ ማን ነገራችሁ? እንዲህ አይነት ንግግር በቂ ማስረጃ ያስፈልገዋል። በጁምዓ ደግሞ ብዙ ነገሮች ተከስተዋል።የታዘዝነው አላህን እንድናወሳ ነዉ እንጂ አደም የተፈጠረበት ቀን በመሆኑ ምክንያት እንድናከብረዉ አይደለም።**“እላንተ ያመናችሁ ሆይ! በዐርብ ቀን ለስግደት ጥሪ በተደረገ ጊዜ ወደ አላህ ማውሳት ሂዱ፤ መሸጥንም ተዉ፤ ይሃችሁ የምታውቁ ብትሆኑ ለናንተ በጣም የተሻለ ነው።”**[32]

5ኛ- (ነቢዩ (ሠ.ዐ.ወ) ሰዎችን አቂቃ እንዲያወጡ ካዘዙ በኋላ ለራሳቸው አወጡ፣ አያታቸው አብዱል ሙጠሊብ ግን በልጅነታቸው አቂቃ አውጥተውላቸዋል።ስለዚህ ሁለተኛ ያወጡት ለአቂቃ ሳይሆን ልደታቸውን ለማክበር ነው!! ምክንያቱም በኢስላም ሁለት አቂቃ የለም፣ አንዱ ልደት መሆን አለበት! ) ይላሉ።

## የዚህ ምላሽ እነደሚከተለው ይሆናል፡-

5.1፡- አያታቸው አብዱል ሙጠሊብ አቂቃ ማውጣታቸው በትክክለኛ ሀዲስ ተዘግቦ አልተገኘም።የተገኘው በጣም ደኢፍ በሆነ ሃዲስ ነው [33]።ስለዚህ ደኢፍ የሆነ ማስረጃ መቁጠራቸው ተገቢም፣ ትክክልም አይደለም።

5.2፡- አቂቃን ለምን የልጅ ልደት እያላችሁ ትተረጉማላችሁ? ይህንን ተፍሲር ያገኛችሁት ከየት ነዉ ? እስኪ አብራሩልን።

5.3፡- አቂቃ የልጅ ልደት ነው ብላችኋል።ልደት በየዓመቱ ማክበር ይቻላል ካላችሁ፤ አቂቃ ለምን ሁለቴ አይደረግም? የሚገርመው ግን አቂቃ አንዴ ብቻ እንዲወጣ ስለተደነገገ ሁለት ጊዜ አይደረግም ካላችሁ በኋላ በጭራሽ አንድም ጊዜ ያልተሰራውን መዉሊድ በየዓመቱ ትሰሩታላችሁ!!

---

[31] ቲርሚዚና አቡዳውድ በዘገቡት ሰሂህ የሆነ ሃዲስ
[32] ቀዱስ ቁርአን 62፡-09
[33] (ኢስቲይአብ የኢብኑ ዐብዱልበርን፣ ሃሺየተል ኢሷባን እና ሱበለል ሁዳ ወረሻድን ይመልከቱ)

5.4:- ነቢዩ (ሠ.ዐ.ወ) ለራሳቸው አቂቃ አወጡ ተብሎ የተገለፀውን ግልፅ[34] ሃዲስ እንደ እናንተ አባባል የመውሊድ በዓል ቢሆን ኖሮ ነቢዩ ለምን በየዓመቱ አልደጋገሙትም?

6ኛ- ሌላው ጠንካራ ማስረጃችን ብለው ከቁርዓን የሚጠቅሱት (የመልእክቱ ትርጉም) :-

**"በአላህ ችሮታና በእዝነቱ በዚህም ምክንያት ይደሰቱ፤ እርሱ ከሚሰበስቡት (ሀብት) በላጭ ነው፤በላቸው::"**

"ራህማ" ብሎ አላህ በዚህ አንቀፅ ላይ የጠራቸው ነቢዩን (ሠ.ዐ.ወ) ነው::ነቢዩ (ሠ.ዐ.ወ) ራህማ ብሎ ጠርቷቸዋል።ስለዚህ በራህማ (ነቢዩ /ሠ.ዐ.ወ/) እንደሰታለን! ይላሉ::

## የዚህ ምላሽ እነደሚከተለው ይሆናል፡-

በሙፍሲሮች ዘንድ በዚህ አንቀጽ ‹‹ራህማ›› የተባለዉ ከዚህ በፊት ባለው አንቀፅ መሰረት ‹ቁርዓን› ነው።አንዳንዶቹ ‹ኢስላም› ብለው ነው የፈሰሩት።"ራህማ" ‹የነቢዩ (ሠ.ዐ.ወ) መልዕክተኛ ሆነው መላክ ነው› ብለው የፈሰሩ ሰዎችም አሉ።ያም ሆነ ይህ በነብዩ መደሰት አስፈላጊ ነዉ።ሰሀቦች ከማናችንም የበለጠ በረሱል ይደሰቱ ነበር።ሆኖም ግን ደስታቸዉን መዉሊድ በማክበር አልገለፁትም።

7ኛ- አቡ ለሃብ የተባለው የነቢዩ (ሠ.ዐ.ወ) አጎት፣ ሱይወባ የተባለች ባሪያው የነቢዩን (ሠ.ዐ.ወ) መወለድ ስትነግረው ነፃ አወጣት[35]:: በዚህም ምክንያት አላህ ሰኞ፣ ሰኞ ቅጣቱን ይቀንስለታል፣ ይህም በቡኻሪን ተዘግቧል ይላሉ::

## የዚህ ምላሽ እነደሚከተለው ይሆናል፡-

7.1:- ቡኻሪ ላይ የተጠቀሰው በዚህ መልኩ አይደለም።ይህ የአቡ ለሃብ ጉዳይ ማንነቱ ባልታወቀ ሰው በሕልም የታየ ነው።ይህንንም ክስተት ያወራው አንድ የሀዲስ አስተላላፊ እንጂ ነቢዩ አይደሉም። የነቢዩ ንግግር ቢሆን ኖሮ እነኳ ይህንን ነገር በማፅደቅ መዉሊድን ካልደነገጉት በቀር ከእሳቸዉ መላክ በፊት የነበረ ክስተት መዉሊድ ለማክበር በምንም መልኩ መረጃ አይሆንም! **በአል** ማለት ደግሞ ተደጋግሞ የሚመጣ ነዉ እንጂ አንድ ግለሰብ ስሜቱን ለመገለፅ ለብቻዉ የፈፀመዉ ተግባር አይደለም።

7.2:- ይህ ሕልም ከቁርዓን ጋር ይጋጫል።አላህ ለሙሽሪኮች ምንም አይነት የቅጣት ቅነሳ እንደማያደርግ ሲገልፅልን እንዲህ ይለናል **"እነዚያን የካዱትም ለነርሱ የገሀነም እሳት አላቸው፤ ይሞቱ ዘንድ በነርሱ ላይ (በሞት) አይፈረድም፤ ከቅጣቷም ከነሱ አይቀለልላቸውም፤ እንደዚሁ ሁሉን ከሓዲ እንመነዳለን::"**[36]

8ኛ- (መውሊድ ምን አጠፋ? ብዙ ሰለዋት እንድናደርግ ይገፋፋናል። የነቢዩን (ሠ.ዐ.ወ) ታሪክ ለማስተማር እድል ይከፍታል።ሰደቃ እንድናበላ ያደርጋል፣ ስለዚህ የጥሩ ነገር በር ከፋች ስለሆነ አትዋጉት) ይላሉ።

## የዚህ ምላሽ እነደሚከተለው ይሆናል፡-

8.1:- ሰለዋት፣ሰደቃ፣ዚክር እና የመሳሰሉት ዒባዳዎች አመቱን ሙሉ ያለገደብ እንዲፈፀሙ በነቢዩ (ሠ.ዐ.ወ) የተደነገጉ ናቸው።ረሱልም

[34] በርግጥ ሀዲሱ ውዝግብ አለበት፤ብዙ ዑለማዎች ሰነዱ ደካማ እንደሆነ ይጠቅሳሉ።
[35] ሱወይባን አቡ ለሃብ ነፃ ያወጣት ነቢዩ (ሠ.ዐ.ወ) ሲወለዱ ሳይሆን ወደ ሂጅራ ከመሄዳቸው በፊት ነው። ኸዲጃ ሱወይባን እንዲሸጥላቸው አቡ ለሃብን ለምነውት ነበር፣ እሱ ግን አልተስማማም። ነቢዩ (ሠ.ዐ.ወ) መዲና ሆነው መልዕክት ይልኩላት ነበር። ይህንንም ኢብኑ ኢስሃቅም፣ ሌሎችም ዘግበውታል።
[36] 35፡-36

ለነዚህ ብዙ መንገዶች እና እድሎችን አመቻችተውልናል።ለምሳሌ አንድ ሁለቱን ብንጠቅስ ፦ ‹‹በጁምዓ ቀን ሰለዋት በእኔ ላይ አብዙ፣ የናንተ ሰለዋት እኔ ፊት ትቀርባለች›› ሌላው ሀዲስ ‹‹አዛን በምትሰሙ ጊዜ ልክ ሙአዚኑ እንደሚለው በሉ፣ እኔም ላይ ሰለዋት አውርዱ፣ በእኔ ላይ አነድ ጊዜ ሰለዋት ያወረደ አላህ በእርሱ ላይ አስር ሰለዋት ያወርድበታል›› እነዚህን የመሳሰሉ እድሎችን ከተጠቀምን ትልቅ ነገር ነው።“በዓመት አንድ ጊዜ” ብቻ መገደቡ ለምን አስፈለገ?

8.2፡- ስለ መውሊድ ጥሩ ጎን ነው ያላችሁትን ትናገራላችሁ፣ በጣም ብዙ የከፉ ተግባሮች ትደብቃላችሁ።እስከ ሽርክ የደረሱ ወንጀሎች እየተፈፀሙበት መሆኑን ከላይ ለማየት ሞክረናል።ካመጣው ጥቅም ይልቅ ቅድሚያ ሰጥታችሁ ማየት የነበረባችሁ ያደረሰውን ጉዳት ነበር።ምክንያቱም ዑላማዎች በአንድ ድምፅ ያፀደቁት መርህ አለ። “ጥሩን ነገር ከማምጣት መጥፎን ነገር መጋፋት ቅድሚያ ይሰጠዋል” ስለዚህ ጉዳቱን መጀመሪያ ተመልከቱ።

8.3፡- የነቢዩን (ሠ.ዐ.ወ) ታሪክ ለመማር በዓመት አንድ ቀን በቂ አይደለም።እውነት ነቢዩን (ሠ.ዐ.ወ) ከወደድን ታሪካቸውን በየእለቱ ጊዜ ሰጥተን እንማር።

9ኛ፡- (ለመውሊድ የታረደን ምግብ ለምን አትበሉም? አላህ ግዴታ አድርጎባችኋል፤ ካልበላችሁ እንደሚቆጣባችሁ በቁርአን እንደዚህ ተገልጿል ይላሉ፡- «በአንቀጾቹም አማኞች እንደ ኾናችሁ (ሲታረድ) የአላህ ስም በርሱ ላይ ከተወሳበት (እንስሳ) ብሉ፡፡›› ስለዚህም በመውሊድ በአል ላይ በመገኘት ለበአሉ የታረዱ ምግቦችን መብላት አለባችሁ) ይላሉ።

## የዚህ ምላሽ እነደሚከተለው ይሆናል፡-

9.1፡- ከላይ የተጠቀሰዉ የቁርዓን አንቀፅ የወረደው ሶሃባዎች እርድን ለመብላት በፈሩ ጊዜ ጥርጣሬያቸውን ለማንሳት ነው።ይህም ቢሆን የሚያመለክተው መፈቀድን እንጂ ግዴታን አይደለም።ግዴታ ያልሆነን ነገር ግዴታ ማድረጉ ትልቅ ወንጀል ነው።ለዚህ አንቀፅ ማብራሪያ (ተፍሲር ኢብኑ ከሲር፣ ኢብኑ ጀሪር አጦበሪ፣ ፈትሁል ቀዲር) የመሳሰሉትን ቢመለከቱ ሃቁን ይረዱታል።

9.2፡- እኛ በአላህ ስም የታረደን አንበላም አላልንም።ነገር ግን መውሊድ ነቢዩ ያልሰሩት ተግባር በመሆኑ ማንኛውንም መሰረት የሌላቸው ዒባዳዎችን እንድንነቅፍ ታዘናል።“ያልታዘዙትን የሚሰሩትን ከቻላችሁ በእጃችሁ፣ በምላሳችሁ ወይም በልባችሁ ታገሏቸው”[37] ተብለን ታዝዘናል።

10ኛ፡- (የአዝሃር ዑላማዎች በሙሉ ድምፅ አፅድቀውታል፣ በሀገራችን የተቋቋመዉ የዑለማዎች የጋራ መድረክም እንዲከበር ወስኗል።ስለዚህ መውሊድ ይፈቀዳል!!) ይላሉ፡-

## የዚህ ምላሽ እነደሚከተለው ይሆናል፡-

10.1፡- አዝሃሮችንም ይሁን የጋራ መድረኩን መመሪያ አድርጎ መያዝ ተገቢ አይደለም ።አዝሀሮች በወሳኝ ጉዳዮች ላይ ያላቸዉ ቸልተኝነት የሚታወቅ ነዉ ፡፡የሰይድና ሁሴንን እና የሰይዳ ዘይነብን ቀብር የሚያመልኩትን እንኳ ግልጽ ተቃውሞ አያሰሙም ። የሁሉም

37 ሰሂህ ሙስሊም

አቋምና ተግባር ማስረጃ አይሆንልንም።**ሰዎች በሀቅ ይመዘናሉ፤ ሀቅ ግን በሰዎች አይመዘንም!!**

10.2፡- ከላይ የተዘረዘሩት መልሶች አዝሃሮችንም ይመለከታሉ።እነሱ ከቁርዓንና ከሀዲስ በላይ አይደሉም።ወደአላህ የምንቃረብባቸውን የአምልኮ ዘርፎች ከአላህ እና ከነቢዩ (ሠ.ዐ.ወ) ውጭ ማንም ቢሆን የመደንገግ መብትና ስልጣን የለውም።ነቢዩ (ሠ.ዐ.ወ) ካልሰሩት ሶሃባዎች ካልሰሩት የሶሶቱ ምርጥ ክፍለ ዘመናት ሰዎች ካልሰሩት ፤ እንዴት ዲን ብለን እንስራው!? አንዳንድ የተሳሳቱ ምሁራን ስለሰሩት ብቻ? ኢስላም እነደሰው ሰራሽ ህግጋት በጉባኤ የሚወሰን አይደለም! ይህ ደግሞ የነሳራዎችና የአይሁዶች መንገድ ነው።

10.3፡- አዝሃሮች በሙሉ ድምፅ አፅድቀውታል የተባለውም ትክክል አይደለም።ከቀደምት የአዝሃር መሪዎች መካከል መሀመድ አብዱ፣ ሸይኽ መራጊ፣ ዓሊ ማሕፉዝ፣ ሀሠነይን መኽሉፍ እና የመሳሰሉት መውሊድን በግልፅ ተቃውመውታል።ከአሁኖቹ ምሁራንም ሸይኽ መሀመድ በረካት፣ አብዱልአዚመል መጥአኒ፣ አብዱል ሙንዒመልበሪይ የመሳሰሉትም በግልፅ ተቃውመውታል።

10.4፡- የሀገራችን ኡለማዎች የጋራ መድረክ ስምምነትን በተመለከተ፤ የሰዎች ስምምነት ግልፅ ከሆኑ መረጃዎች ጋር እስከተጋጨ ድረስ ቦታ አይኖረዎም። በመረጃ ባልተደገፈ መልኩ አክብሩ ቢሉ ተቀባየነት አይኖረዉም፡፡ በጋራ መድረኩ በመታቀፍ ፊርማቸዉን ያኖሩት ሰዎች ብዙ እንደሆኑ ሁሉ ብዙዎችም በወቅቱ የተቃዉሞ ድምፃቸዉን አሰምተዋል፡፡ እንደሚታወሰው በዘጠኝ ክልሎች የሚገኙ የሙስሊሙ ተወካዮች ስምምነቱን በመቃወም መግለጫ አዉጥተዋል።

11ኛ፡- (መውሊድ ብናከብር ምን አለበት? ለምሥጋና ብለን ነው የምናከብረው) ይላሉ።

## የዚህ ምላሽ እነደሚከተለው ይሆናል፡-

አንድ ሰው አል-ኢማሙ ማሊክ ዘንድ መጥቶ ከየት ነው ኢህራም የማደርገዉ? ሲላቸው ረሱል ካሰሩበት ከዙል ሁለይፋ! አሉት።እኔ ምፈልገው ከቀብራቸው መሀረም ነው አላቸው።አታድርግ ፈተና እፈራልሀለሁ አሉት።‹ ይህ ምን ፈተና አለበት? ሲል ጠየቃቸዉ› ጠቂት ርቀት እኮ ነው የጨመርኩት አላቸው "ረሱል ያልደረሱበትን መልካም ስራ በመስራት ቀዳሚ መሆንህን ከማሰብህ የበለጠ ምን ፊትና አለ?! አሉና ሱረቱ ኑር ላይ ያለውን አንቀፅ ጠቀሱ፤ (የአማርኛ መልዕክቱም፡- « ትዕዛዙን የሚጥሱ መከራ እንዳትደርስባቸው ወይምአሳማሚ ቅጣት እንዳያገኛቸው ይጠንቀቁ፡፡»[38]

12- ሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚያህ መዉሊድን ማክበር አጅር(ምንዳ) ያስገኛል ብለዋል።

## የዚህ ምላሽ እነደሚከተለው ይሆናል፡-

12.1፡- ሸይኹል ኢስላም ያሉት ይህንን ነዉ ‹‹ **አንዳንድ ሰዎች መዉሊድን ያልቃሉ ፤ እንደበአልም ያከብሩታል።ይህንን የሚያደርጉት ከመልካም ኒያና ረሱልን ከማላቅ የተነሳ ነዉ።በዚህም ታላቅ ምንዳ ያገኙበታል።››**39

12.2፡- ሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚያህ ለንግግራቸዉ ከቁርአንና ከሱና መረጃ ይፈለገለታል እንጂ ንግግራቸዉ በራሱ መረጃ ተደርጎ አይወሰድም!!

---

[38] ቅዱስ ቁርአን 24፡-63
[39] ኢቅቲዷኡ ሲራጥ አል-ሙስተቂም ገፅ 297

12.3፡- እኚህ ታላቅ አሊም ይህንን ንግግራቸዉን በዚሁ መፅሀፍ ላይ አብራርተዉታል፡፡‹‹ እንደዚሁ አንዳንድ ሰዎች ፤ ክርስቲያኖችን በዒሳ ልደት በመፎካከር ወይም ለነብዩ (ሰ.ዓ.ወ) ካላቸዉ ዉዴታ በመነሳት የሚፈጥሩትን (ቢድዓ) በተመለከተ፤ አላህ ሰለ ዉዴታቸዉና ጥረታቸዉ ሊመነዳቸዉ ይችላል፡፡በቢድዓዉ ግን አይመነዳቸዉም!!››[40]

12.4፡- ሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚያህ በመፅሀፎቻቸዉ በተለያዩ ቦታዎች ላይ መዉሊድ ማክበር እንደማይፈቀድ ተናግረዋል፡፡ለምሳሌ፡- **‹‹ የበአል ወቅት ተደርጎ ያልተደነገገን በአል አድርጎ መዉሰድ ፤ ለምሳሌ ፤ በረቢዑል አወል የመዉሊድ ለሊት ተብለዉ እንደሚከበሩት አይነት … ሁሉም የዚህ ኡማህ አበዉ ትዉልዶች መልካም አድርገዉ ያላዩትና ያልሰሩት የቢድዓ ተግባር ነዉ››**[41]

## መደምደሚያ

- በአንድ ርዕስ ላይ ሁለት የሚጋጩ ሀሳቦች ትክክል መሆን አይችሉም፡፡የነቢዩ (ሠ.ዐ.ወ) ቃል ብቻ ነው ትክክሉ፡፡ከዚያ ውጭ ያለና ከነቢዩ (ሠ.ዐ.ወ) ቃል ጋር ከተጋጨ ውድቅ ነው!
- መውሊድ ያላከበርነው ነቢዩን (ሠ.ዐ.ወ) ወደን ፈለጋቸዉን ተከትለን እንጂ እርሳቸዉን ጠልተን አይደለም፡፡
- ያልታዘዘውን ነገር የተወ ሰው ማንም ሊወቅሰው አይችልም፣ የሠራ ሰው ግን ራሱን ለአደጋ አጋልጧል፡፡
- አንድ ሰው አዲስ ማንም ያልሠራውን ስራ ሰርቶ ማስረጃ ከቁርዓን ውስጥ ቢፈልግ ሰዎችን የሚያምታበት ነገር ማግኘት ይችል ይሆናል፡፡የሚመሳሰል ነገር ማግኘት ግን ትክክለኛ መረጃ ማግኘት አይሆንም፡፡
- ማንኛውንም ተግባር ስንፈጽም የዲን ጉዳይ ከሆነ ነቢዩ (ሠ.ዐ.ወ) አዘውብታልን? የዱንያ ጉዳይ ከሆነ ደግሞ ነቢዩ (ሠ.ዐ.ወ) ከልክለውታልን? የሚሉትን ጥያቄዎች ማንሳት ይኖርብናል፡፡ ምክንያቱም የዲን ጉዳይ ያልታዘዝንበት ከሆነ መጤ ነው! ቢድዓ ነው፡፡የዱንያ ጉዳይ ሆኖ ያልተከለከልንበት ከሆነ ግን የተፈቀደ ነው፡፡ **«ለነርሱ ምን እንደተፈቀደላቸው ይጠይቁሃል፤ ለእናንተ መልካሞች ሁሉና ተፈቀደላችሁ፣ በላቸው»** [42]

__በመጨረሻም፡-__ ነቢዩ እንዲህ ይላሉ፡- **"ሕዝቦቼ ለ 73 ይከፋፈላሉ፤ ሁሉም የእሳት ናቸዉ አንዱ ቡድን ሲቀር፣ እሱም እኔና ሰሀቦቼ ያለንበት መንገድ ላይ ያለዉ ቡድን ነዉ"**[43]

ከእሳት ቡድኖች ላለመሆን የነቢዩ (ሠ.ዐ.ወ) እና የሶሃባዎችን ሥራዎች የቻልነውን ያህል መከታተል፣ ያልሠሩትን መተው ይኖርብናል፡፡በዚህ ጉዳይ ላይ ካላቸዉ ለዘብተኛ አቋም በመነሳት "የመዉሊድ ጉዳይ ሊያወዛግበን አይገባም! እንቻቻል!" በማለት ህብረተሰቡ ሀቅን እንዳይረዳ መሰናክል የሚሆኑ ወገኖች አላህን ሊፈሩ ይገባል እንላለን፡፡ሀቅን መርዳት ግዴታ እንደሆነ ልብ ይበሉ፡፡አንድ ነገር ሀቅ ወይም ባጢል መሆኑ የሚለየዉ ከትክክለኛ መረጃ በመነሳት እንጂ በጋራ ጉባኤዎችና ስምምነቶች አይደለም፡፡የነብዩ ወደጅ ፤ ፈለጋቸዉን ተከታይ የሆን ሱኒይ ሰዉ ለስሜትና ዝንባሌ ቦታ ሊሰጥ አይገባም፡፡አቡበከር ኢብኑል-ዓያሽ ‹ሱኒይ ማን ነዉ?› ተብለዉ ሲጠየቁ

---

[40] ኢቅቲዷኡ ሲራጥ አል-ሙስተቂም ገፅ 294
[41] አል-ፈታዋ 25/298
[42] ቅዱስ ቁርአን ል-ማኢዳህ ቁ.4
[43] የዚህ ነቢያዊ ሀዲስ መልዕክት ከበርካታ ሰሃቦች በተለያዩ መንገዶች የተዘገበ ነው፡፡

‹የፈጠራ መንገዶች ሲጠቀሱለት ለንሱ ምንም ወገንተኝነት የማያሳይ ነዉ›[44]

በማለት መለሱ፡፡

አላህ ሁላችንንም ወደ ቀጥተኛዉ መንገድ ይምራን!!

# ናጂያ ኢስላማዊ ማህበር

አድራሻ- ለይላ ህንፃ አምስተኛ ፎቅ ቢሮ

ቁጥር 33

ፖስታ 183883

ስልክ +251-112-758398

ሞባይል +251911402889

ፋክስ - 251-11-2758399

አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ

[44] ኪታብ አሸሪዓ ሊልአጁሪይ ቁጥር 2058